# በስያትል ከተማ የተካሄደው የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ጉባዔና እድምታው

ክፍል አራት

ታምራት ይገዙ

August 16, 2017



Ethiopian National Unity Convention in Seattle.

ታምራት ይገዙ –

ክፍል አራት

ወደ ክፍል አራት ከማቅናቴ በፊት አንባቢን ይቅርታ እጠይቃለው ምክንያቱም በክፍል ሁለት ጹሁፊ ላይ "የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅንቅቄ ውስጥ ያሉት ድርጅቶች ብቻ የኢትዮጵያን ችግር ፈቺዎች ሆነው ሲያቀርቡ አንድም የአገራችንን ችግር በጥልቀት አልተረዱትም አሊያም ህወሀት በፓሪሱ ጉባኤ ላይ የሰራውን ደባ ለመኮረጅ በዝግጅት ላይ ናቸው ማለት ነው:: ህወሀት በደርግ መውደቂያ ሰሞን በተጠራው የፓሪሱ ጉቤኤ ላይ ያደረገውን ደባ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሚያውቀው እዚህ ላይ መግለጹ ፋይዳ የለውም ::" ይላል "የፓሪሱ ጉባኤ" የሚለው የእንግሊዙ ጉባኤ ተብሎ ይነበብልኝ ለተፈጠረም ስህተት አንባቢን በድጋሚ ይቅርታ እጠይቃለው::

"እንዳያምህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው::"

በስያትል ከተማ በተካሄደው የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ስብሰባ ላይ ሌላው ተናጋሪ ፐ/ር ጌታቸው በጋሻው ሲሆኖ እሳቸውም እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል

"ኦሮሞ ለምሳሌ ተደራጅቶ መጥቶል እራሱን ወክሎ ኦሮሞ ብሎ የኦሮሞ ዲሞክራት ፍሮንት ትልቅ ፍርሃትን ነው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ የጣሉት የነበሩትን በደሎች አንስተን አስተካክለን ቅድም ዶ/ር በያን ኢሊኮንትሊ ሲገልጹት የነበረውን ትላንት ዶ/ር ሌንጮ በሚያስደስትን ደረጃ ሲገልፁልን የነበሩትን ለማድረግ ቆርጠው ሲመጡ ይህ ኤ ብሪክ ስሩ (A Breakthrough) በኢትዮጵያ ፖለቲካ የምንለው በተባበረ እንድ በሆነች እትዮጵያ ውስጥ ሁሉም በእኩልነት የሚኖርባት አገር ለመመስረት የኢትዮጵያ አገራዊ ነናቄን ከፈጠሩት አራት ድርጅቶች ውስጥ ኦሮሞ ዲሞክራት ፍሮንት አንዱ ነው በመቀጠልም ግንቦት ሰባት; የሲዳማ ዲሞክራሳዊ ንቅናቄ; እና የአፋር ህዝቦች ፓሪት ይህንን ንቅናቄ መስርተዋል::

ይህንን አገራዊ ንቅናቄን ሲመሰርቱ ያስቀመጦቸው ቡዙ የተወሳሰቡነገሮች አይደሉም ሶስት ዋና ጥያቄዎች ናቸው

1 ኛ እትዮጵያ የምትባል አገር አለች ትቀጥላለች

2 ኛ ሁለንተናዊ መፍቶች ይከበራሉ

3 ኛ የስልጣን ምንጭ የሚሆነው በማንኛውም በመንግስት ደረጃ በህዝብ ምርጫ ወይም በህዝብ ድምጽ ብቻ ነው::

ይህንን National consensus ናሽናል አጀንዳ አለን ወይ ሲባል ይህ እኮ ዩንቨርሳል ዲሞክራሲ ከተባለ ይህ ነው ይህንን አዳፐት ያደረገ ይህንን የወሰድ የፖለቲካ ድርጅት ይህውና ተፈጥሮል አለ በዚህ ነው የሚያምኑት ካለ ቦሃላ በነኝህ ሁሉ የሚያምን አሁን

ለምሳሌ ዶ/ር አረጋዊ እዚህ አሉ እሳቸው ያሉበት አንድ ስብስብ አለ ሸንጎ የሚባል ይህንን አይቶ መልስ ቢመልስ ጥሪ ይመስለኛል ወደፊትም የሚፈጠሩ ድርጅቶች ካሉ በዚሁ ቢቀጥሉ ጥሩ ይመስላኛል የአማራውን መደራጀት የምቃወሙ ሰዎች አሉ መቃወም አንችልም እኔ በነገራችን ላይ የአማራ ወኪል አይደለሁም የማንኛውም ፓሪቲ አባል አይደለሁም አማራን አደራጃለው እያልኩ አይደለም አማራ ቢደራጅ የሚያስፈራን ምን ነገር አለ?"::

የፖለቲካ ባህላችን ከጅምሩም ያላማረበት በሂደትም መሻሻል የማይታይበት ሆኖ ዛሬም በትናንቱ መንገድ ከመንጎድ መውጣት ባለመቻላችን ለህወሀት እንደተመቸን አለን፡፡ ብልሹው የፖለቲካ ባህላችን ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ሌላው ሲናገረው ወይንም ሲሰራው ወንጀል ያልነውን እኛ ስንሰራ ስንናገረው እንደ መልካም ነገር ይታይልን መባሉ ነው፡፡

በአሁኑ ዘመን ይህ ችግራችን መፍትሄ አለማግኘቱ ነው ሁላችንንም እያሳሰበን ያለው በቀደሙት አመታቶች ማለትም በ 1960 እስከ 1990 አ/ም ምንልባት የአይዶለጂ ችግር ስለነበረ ነው ይባል ከ 1990 ቦሃላ ግን የአይዶለጂ ችግር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ቦታ ያላቸው አይመስለኝም:: ምናልባት ሊሆን የሚችለው ከ 1990 ዎቹ በፊት የያዙትን አይዶለጂ ከውስጣቸው ሊያጠፉት ያልቻሉ አንዳንድ ወንድሞቻችን ስላሉ እነዚህ ወንድሞቻችን የምጠይቀው "ከመጠምጠም መማር ይቅደም "እንደሚባለው ሁሉ እናንተም ድርጅቶች አብረው እንዲሰሩ ለማቀራረብ ከማሰባችሁ በፊት በውስጣችሁ ያለውንና የቀየውን የአይዶለጂ እርሾ ሙሉ በሙሉ ከውስጣችሁ ማውጣት ይጠበቅባችኋል እላለሁ ይህን ከደረጋችሁ መሪ ድርጅት አሊያም አውራ ድርጅት የማውጠት ህልማችሁ ከውስጣችሁ ይወጣል መለት ነው:: ይህንን አስካለደረጋችሁ ድረስ ኢትዮጵያዊው ሁሉ " ደሞት መልኩሳ አመላን አትረሳ" እንደሚላቸው ልትገነዘቡ ይገባል:: ይህ በውስጣችሁ ያለውን የአውራ ድርጅት የማውጣት ቅዠትና ያንን የቆየ የአይዶለጂ እርሾ ከውስጣችሁ ሙሉ በሙሉ ካለስወጣችሁ በስተቀር የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ በተለይ የዘመኑን ወጣት ልብ እንደማተገኙት ልትገነዘቡ ይገባል እንደሚነገረው በአሁን ግዜ ያለው የአገራችን ወጣት 65 በመቶ እንደሆነ ይገመታል::

እርግጥ ነው ህወሓት በአገራችንና በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰው በደል እጅግ የከፋ በመሆኑ ሁላችንም በያለንበት ሆነን እንቆጫለን; እንበሳጫለን በዚህም የተነሳ አንድ ግለሰብ አምስት ስድስት ተቆም ውስጥም ሆነ ድርጅት ውስጥ እየገባ ስራ ለምሰራት ሲሞክር ይታያል በእኔ እይታ ይህ ራሱ ከውጤቱ ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ ትግሉን የሚያቀጭጨው አንዱ ክፍል ነው ባይ ናኝ ምክንያቱም "ዘጠኝ ዳቦ ከመላስ አንድ ዳቦ መብላት ያጠግባል ይባል የለ":: የህወሓት ድርጅት በአገር ቤት ባሉ የሰላማዊ ትግል ድርጅቶች ውስጥ እየገባ ድርጅቱን እንደሚያፈርሰው ሁሉ ውጪ ሀገር ሆነው የአገር ቤቱን ሰላማዊ ትግል የሚረዱ ድርጅቶች ወስጥ እየገቡ እንቅፋት የሚፈጥሩ የአውራ ድርጅትነት መንፈስ የተጠናወታቸው የድርጅት መሪዎችና አባላቶች በየአገሩ ይታያሉ እነሱ ከሌሉበት ምንም አይነት ድጋፍ ሰጪ ታክስ ፎርስ አይቆቆምም እንዳይቆቆም ለት ተቀን እንቅልፍ አጥተውና ተግተው የሚሰሩ በየከተማው እናያለን እነዚህም የድርጅት መሪዎችና አባላቶች ቆም ብለው ቢያስቡ ጥሩ ነው ባይ ነኝ ምክንያቱም ይህ አይነቱ እኛና እነሱ የሚለው ይፖለቲካ እሽቅድምድሞች ትግሉን ሲጎዳ እንጂ ትግሉ አንድ እርምጃ ወደፊት ሲያራመድ አልታየም::

ወደትነሳሁበት ወደ ሲያትሉ ጉባኤ ስመለስ ለምሳሌ የተከበሩ ፐ/ር ጌታቸው እንዲ ሲሉ ተናግረዋል "ዶ/ር አረጋዊ እዚህ አሉ እሳቸው ያሉበት አንድ ስብስብ አለ ሸንጎ የሚባል ይህንን አይቶ መልስ ቢመልስ ጥሩ ይመስለኛል ወደፊትም የሚፈጠሩ ድርጅቶች ካሉ በዚሁ ቢቀጥሉ ጥሩ ይመስላኛል "

ይህንን የመሰለ ጥሪ የተከበሩ ፐ/ር ጌታቸው በጋሻው ለሸንጎ አባልና ለድርጅቱ ጥሪ ሲያደርጉ የተለያዩ ጥያቄዎች በውስጤ ተመላለሱ እነዚህን ጥያቄዎች እርሶ እራሶት ለእራሶት ሂልና እንዲመልሱ ለመጠየቅ ተገደድኩ ጥያቄዎቼም

(1 ኛ) የኢጋራችንን ውስብስብ ችግርና ለመፍታት ቢያንስ ከአገር ውጪ ያሉትን ድርጅቶችን በ National consensus (ናሽናል አጀንዳ )ለመቅረጽ የምታስቡ ታዋቂ ግለሰቦች እንዴት ነው ለተለያዩ ድርጅቶች የአቀራረብ ከበሬታ ያላችሁ? እናንተ ሽምግላችሁ ለማቀራረብ የምታስቡ ታዋቂ ግለሰቦች በተለያየ ሚዲያ ላይ ቀርባችሁ ስትናገሩ አድማጭ ምን ይለናል የሚል ጥያቄ በውስጣችሁ አይጭርም?::

(2 ኛ)የተከበሩ ፐ/ር ጌታቸውም አረ ለመሆኑ ለሌሎች አራት ድርጅቶች ኑና ተሰባሰባችሁ አገራዊ ንቅናቄውን መስርቱ ስትሉ እርሶ የሸንጎ መሪዎችንና የሸንጎን ሙለ አድራሻ የሎትም ነበር ማለት ነው ለሸንጎ አባል ለሆኑት በዶ/ር አረጋዊ በኩል በሲያትሉ ስብሰባለይ ለድርጅቱ ጥሪ ያደረጉት? እንደዚ ዓይነት የችግር አፈታትና ሽምግል አለወይ? ይህን ዓይነቱ ሰራ በአገርና በህዝብ ላይ ግፍ መፈጸም አይሆንም ይላሉ?

ለመሆኑ ከስህተ ለመማር አርባ ዓመት አይበቃም ይላሉ? ካልበቃስ ከአሁንስ ቦሃላ ስንት ዓመት ይፈጅብናል ከስህተታችን ለመማር ውይስ ነገሩ "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይነቃም" እንደሚባለው ይሆን:: ድሮ ድሮ አባቶቻችን " የተማረ ይግደለኝ" ይሉ ነበር ምክንያቱም የተማረ ከመግደሉ በፊት ያመዛዝናል ብለው ያስቡ ስለነበር እነዛ አባቶቻችን አሁን ሰዓት ላይ ኖረው የሚደረገውን ቢመለከቱ ሀሳባቸውን ለውጠው "የተማራ ገደለኝ" የሚማረሩ ይመስለኛል እርግጥ ነው ሁለቱም መሞቶትን ቢያመላክቱም

የመጀመሪያው አማሞት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተና የተማሩትም አስተዋይ ልቦና እንደነበራቸው የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ግን የማስተዋል ብቃታችን ከውስጣችን ተሞጦ እንደወጣ የሚያሳይ ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ የሀገራችን እና የህዝባችን መከራና ስቃይ ልባችንን ቢነካን ኖሮ የተከበሩ ፐ/ር ጌታቸው ለሸንጎ አባል ለሆኑት ለዶ/ር አረጋዊ ጥያቄ ማቅረብ የነበረባቸው የሲያትሉ ጉባዬ ላይ ሳይሆን ሌሎችቹን አራት ድርጅቶች ማለትም ኦሮሞ ዲሞክራት ፍሮንት; ግንቦት ሰባት; የሲዳማ ዲሞክራሳዊ ንቅናቄ; እና የአፋር ህዝቦች ፓሪቲ አገራዊውን ንቅናቄውን እንዲመሰርቱ ሲጋበዙ ዶ/ር አረጋዊ ላሉበት ድርጅት ኑ አብራችሁ ስሩ ብለው አብረው አገራዊውን ንቅናቄ እንዲመሰርቱበቅንነት ይሰሩ ነበር ያንን ዓይነት ጥረት አድርገው ቢሆን ኖሮ በመላው አለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያኖች በሙሉ ይህ ነው ሽምግልና ይህ ነው ለህዝብ መቆርቆር ይህ ነው ከእኛና ከእነሱ ከሚባለውና ከፖለቲካ ጥልፍልፎሽ እራስን ማጽዳት በማለት ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአንድ ድምጽ በመሆን ድካማችሁን ፈጣሪ ይቁጠርላችሁ በማለት ለድካማቸው እውቅና በመስጠት የሚገባችሁን ከበሬታ ያቀርብላችሁ ነበር:: ይህ ሲሆን ግን አልታየም ለዚህም ቡዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ለምሳሌ አንዳንድ ወንድሞች ከአፍላ ጉርምስናቸው ዘመን አንስተው የድርጅት አባልና ካልተሰሳትኩኝ በአመራርም ድደረጃ ሲደክሙበት ሲታገሉበት የነበሩበት የኢሕአፓ ድርጅት በሁለት በመከፈሉ የተነሳ ያሰቡትን የስልጣን እርከን ባለማግኘታቸው ይሁን አሊያም ሌላ ምክንያት ጥርስ የነቀሉበትን ድርጅትና የትግል አገሮቻቸው ጋር በጡሩ እንደማይተያዩ የሚታወቅ ነው በዚህም የተነሳ ያ የነበሩበትን ድርጅት ከሌሎች ጋር ተባብሮ መስራቱን በጥሩ ዓይን አያዩትም ስለሆነም በሱ የተነሳ ሌሎችን ድርጅት ጭምር ሲጎዱ ይታያሉ የሚያሳዝነው እነዚህ ወንድሞች ይህ ሲያደርጉ አጣቃላይ ትግሉን እንደሚጎዳ አለመግንዘባቸው ነው::

ይህ ባልተደረገበትና ቁጥራቸው ከአስር የሚበልጡ የህዝባችንና የአገራችን ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ድርጅቶች በዊጪው አለም እያሉ እነሱን ግንዝቤውስጥ ሳያስገቡ የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ መመስረትና ግንቦት ሰባትን በአውራነት ለማውጣት ስድስት ወርና ከዛ በላይ ግዜ መፍጀት በራሱ ትልቅ ስህተት ነው ባይ ነኝ::

ፐ/ር ጌታቸውም ሆኑ ሻ/ቃ ዳዊት እውነተኛ የሃገር ሽማግሌ ሆኖው የተራራቁትን አቀራርበው ቢሆን ኖሮ ሁላችንም ከመቀመጫችን ተነስተን እክብሮታችንን እንለግሳቸው ነበር እነሱ የሰሩት ግን “እንዳያምህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው” የሚያስብል ስራ በመሆኑ የአገራዊ ንቅናቄው ጥንሡ ከወዲሁ ጌሾ በዝቶበት መሮል አሊያም ብቅል አንሶት ቀጥኖል ማለት ነው ስለዚህ የቀረ ድፍድፍ ካላችሁ አልሱትና የዶሮ ዓይን የመሰለ ጠላ ጠምቃችሁ አሽናፊና ተሸናፊ የሌለበት በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ በውጪ አገር ያሉ ድርጅቶች ሁሉ ከአንድ ዋንጫ እየተጎነጩ አገራችንን ኢትዮጵያን ከህወሀት የባርነት ቀንበር ለማላቀቅ አዲስ ቃል ኪዳን እንዲገቡ ለአገርና ለህዝብ ስትሉ በሰከነና በተረጋጋ ሂሊና ምከሩ ያን ግዜ ሁሉም አሻናፊዎች ሆነው ይወጣሉ ማለት ነው ያ ካልሆነ ግን ድካማችን ሁሉ “ወሃ ቢወቅጡት እንቦጭ: እንደ ማለት ነው::

በሌላ በኩል በተከታታይ ጹሁፊ ልገልጸው እንደሞከርኩት እኛና እነሱ ከሚለው ከቆየና ካፈጀው የፖለቲካ አመለከከት ሁላችንም እራሳችንን ማራቅ አለብን የሚል እምነት አለኝ በተለይ በተለይ ታዋቂ ግለሰቦች; የድርጅትም ሆነ የንቅናቄ መሪዎች እና እንዲሁም ተመሪዎች ይህን የቆየና በአሁን ሰዓት ተቀባይነት የሌለው የአይዶለጂ አመለካከትይዞ በአካሄድና በአመለካከት የተለያዩትን ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦችን ለማቀራረብ ማሰብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስለኛል ስለሆነም ለወጥ ከያንዳንዳችንና መጀመር ያለብን ይመስለኛል::

ስለ መለወጥ ጉዳይ ከአንድ ወዳጄ ጋር ሳወራ እንዲህ ያለኝን አልረሳውም ይህ ወዳጄ ያወጋኝ እንዲህ ነበር “በአንድ አደራሽ ውስጥ በቡዙ መቶዎች የሚቆጠሩ በአገራቸው ላይ የአስተዳደር ለውጥ አሊያም የሲስተም ለውጥ የሚሹ ለውጥ ፈላጊዎች ተሰብሰበዋል የእለቱ እንግዳም ስለለውጥ አስፈላጊነትና ለውጥ ቢከሰት ጥቅሙንና ጉዳቱን ከተለያየ አቅጣጫ እያመላከተ ካወያየ ቦሃላ ለተሰበሳቢው ህዝብ ሁለት ጥያቄ አቀረበ የመጀመሪያው ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር አሁን እዚህ ከተሰበሰብነው ውስጥ “ለውጥ” እንዲመጣ የምንፈልግ ሰዎች እጃችንን እናውጣ አለና እርሱም እጁን አወጣ በአደራሹ ውስጥ ያሉት በሙሉ እጃቸውን አውጡ እሱም በመገረም በጣም የሚገርም ነው ሁላችንም ለውጥ እንፈልጋለን ማለት ነው ይህም ጥሩ ምልክት ነው ለውጥ ለማምጣት ካለ ቦሃላ ሁለተኛውን ጥያቄ እንዲህ በማለት ጠየቀ እስቲ አሁን ደሞ “ለመለወጥ” የተዘጋጃችሁ ሰዎች እጃችሁን አንሱ ብሎ የራሱን እጅ አወጥ በዚህ ግዜ በአዳራሽ ውስጥ የሚታየው አንድ የራሱ እጅ ብቻ ነበር ሌሎቹ ሁሉም ወደ መሬት አቀርቅረው ሃሳብ ውስጥ የገቡ ይመስሉ ነበር” ይህንን ያ ወዳጄ ሲያጫውተኝ የገዛ ሂሊናዬ እኔኑ ስለ መለወጥ እራሴን እየጠየኩኝ ነበር:: እርግጥ ነው መለወጥ ከራስ ይጀምራል አልኩኝ በሎሆሳስ::

ይህን ሳይሆን ቀርቶ በውስጣችን ያለው የቆየና የኮመጠጠ የአይዶሎጂ እርሾ ከውስጣችን አውጥተን ሳንደፋ ድርጅቶችን አነቀራርብ የምንል ከሆነ እያጠፋን ያለነው አውቀን እንጂ ሳነውቅ አይደለም ማለት ነው ይህ ደሞ ለለፉት አርባ አመት የተጎዝንባቸው የእሻከ መንገድ ስለሆነ መቼ ነው ከዚህ ዓይነት አባዜ የምንላቀቀው ብለን እራሳችንን መጠየቅ መጀመር አለብን ማለት ነው? እርግጣኛ ነኝ እኔ ሰውን የድርጅት አባል አይደለሁም ብዬ ላሳምንና ልሸፍጥ እችል ይሆነል ሂኒናዬን ግን መዋሸት የምችል አይመስለኝም ስለሆነም እያንዳንዳችን በሂሊናችን ተጠያቆዎች እንደሆንን ማወቅ አለብን ባይ ነኝ::

ይህ የድርጅት አባል አይደለሁም እያሉ በድብቅ ግን ያለንበትን ድርጅትን የምንረዳ የሌለንበትን ድርጅትና ታክስ ፎርስ የምናዳክምና የምናፈርስ ግለሰቦች በየከተማው በብዛት ስላላን ይህ ደሞ ህወሀት በአገር ቤት ውስጥ ያሉትን ተፎካካሪ ድርጅቶች የሚያጠቃበት መንግድ ስለሆነ እኛም በውጪ አገር እየኖርን በድርጅቶችና በታክስ ፎርሶች ላይ ያንን ዓይነት ደባ የምንፈጽም ከሆነ ለምንድን ነው ህወሀትን የምንወቅሰው ብለን እራሳችንን መጠየቅ ያለብን ይመስለኛል ምክንያቱም እኛም የአገር መምራቱን እድሉን ባናገኝ ነው እንጂ እድሉን ብናገኝ ይህኑኑ በግልጽ ሳንሰራ የምንቀር አይመስለኝም ምክንያቱም ስልጣን ላይ ሳንወጣ እየሰራን ያለነው ስራ ህወሀት በአገር ቤት እየሰራ ያለውን ስራ በመሆኑነው ነው ብል ያጋነንኩኝ አይመስለኝም::

ይህ ጉዳይ ድርጅቶችን እንደድርጅት ገለሰቦች እንደግለሰብነታችን ሁላችንንም የሚመለከት ከችግሮቻችን ውስጥ አንዱ ስለሆነ በድፍረት ልንነጋገርበት ከሚገባቸው ችግሮቻችን ውስጥ አንዱ ነው ብዬ አስባለው:: የሰው ልጅ በእውቀቱ መጠን ያስባል ባሰበው መጠንም ስራውን ያከውናል ለማወቅ ደግሞ መማር ብቻ አይጠቅምም። የሰው ልጅ ከትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከስህተትም ይማራል ይባላልና ምን ያ ብቻ መማር የፈለግ ሰው እንኮን ከወቀሳ ከስድብ ይማራል ይባል የለ። የአብዞኞቻችን ችግር "ሲወለድ ያጠለቀውን ሲሞት አወለቀው" እየሆነብን ይመስለኛልና እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን የግድ መሞት የለብንም ቀድመን ያጠለቅነውን ለማውለቅ::

እርግጥ ነው በፖለቲካ ጉዞ ቅንነት የሚታሰብ አይደለም በተለይ በእኛ አገር ሁኔታ ነገር ግን የተጎዘንባቸውን የችግርና የመከራ አመታቶች ግምት ውስጥ አስገብተን ትላንት የሄድንበት መንገድ ጥሩ አለመሆንን እያወቅን ዛሬ የምንደግመው ከሆነ እኛ ኢትዮጵያዊያን ያላወቅነው ችግር አለብን ማለት ነው:: በጣም የሚገርመው ከአገራችን ወጥተን በሰለጠነው አለም የምንኖር ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሰለጠነው አገር በመኖራችን ብቻ ልንማረው የሚገባ ነገር አለ ብዬ አስባለው በሌላ በኩል እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው ከፍተኛ ተቆማት ውስጥም በመግባት በቀሰሙት እውቀት አንቱ ተብለውና ተከብረው ሰርተው የሚያሰሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ትውልደ ኢትዮጵያኖች እንዳሉን ሳልጠራጥር መናገር እችላለው በነዚህም ሰዎች ከልቤ እኮራለሁ:: እኔን ያልገባኝ ነገር ቢኖር በአገራችን በኢትዮጵያ ላይ ቢያንስ በእኔ እድሜ እንኮን ለደረሰው ችግር መፍትሄ አለመገኘቱ ነው:: በሌላ በኩል ችግሩ ሳይታወቅ ቀርቶ ቢሆን እንኮን ጥሩ ችግሩ ግን እንደታወቀ ሁሉም ይስማማል ይህ ከሆነ እንግዲህ መፍትሄ እንዳያገኝ እየሰራን ያለነውና ችግር እየፈጠርን ያለነው እኛው ነን ማለት ነውን?::

" ተያይዘን መራመድ ካልቻልን ተያይዘን መውደቅ ነው የሚቀጥለው ይህ ደሞ እንደ አንድ ዜጋ አንደ ትውልድ ሁላችንንም የሚያሳስብ ነገር ነው:: ወደ ሚቀጥለው ነገር ለመሄድ መጀመሪያ መጥራትና መስራት ያለበት ነገር አለ ለዚህ ሁሉ ሁሉንም ትውልድ ሊያሳትፍ የሚገባ ከምንም በላይ ደሞ ታላላቅ ወንድሞቻችን ሊያስቡበት የሚገባ እኛን መንገድና አቅጣጫ የማሳየት ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ነው::" ቴዲ አፍሮ ለ VOA ጋዜጠኛ ለአቶ አሉላ ከሰጠው ቃለ መጠይቅ የተወሰውድ

እኔም እንደ ወንድማችን እንደ አሪትስት ቴድሮስ ካሳሁን ያ ትውልድ እያልን የምንጠራችሁ ተላላቅ ወንድሞቻችን ለተናናሽ ወንድሞቻችሁ የምታወርሱቸው ምንድን ነው? ታናናሽ ወንድሞቻችሁ የናንተ ትሩፋት ምንድን ነው እስቲ ንገሩን ቢሎችሁ መልሳችሁ ምንድን ነው?

በመጨረሻም:

በስያትል ከተማ የተካሄደው የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ጉባዔና እድምታው በሚል ለተከታታይ የጻፍኩት ጽሁፍ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ለመኮነንና ለማጥላላት ሳይሆን ሁላችንም የአገራችን የኢትዮጵያ ነገር ስለሚያሳስበንና ስለሚያገባን በግልጽነት ላመነጋገርና ለመወቃቀስ በሚል ህሳቤ እንደሆነ እንድትገነዘቡልኝ ከወዲሁ አሳስባለው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ተወልደን ያደግንበት በሃልና መህበረሰብ "ንጉስ እይወቀስ ሰማይ አይታረስ" እየተባለ ስለሆነ ያደግነው እንኮን ንጉስን አይደለም ታላቅን ወንድም አሊያ ታላቅ እህትን መውቀስ እንፈራለን ስለዚህ በእኔ እምነት መወቃቀስ መጥፎ አይደለምብዬ ስለማስብ መወቃቀስን አንፍራው እኔም ለመወቀስና ለመታረም ዝግጁ ነኝ በሌላ በኩል መወቃቀስ ማለት መሰዳደብ እንዳልሆነ ሁላችንም እንገነዘባለን የሚል እምነት አለኝ:: ስለሆነም አውቄ በድፍረት ሳለውቅ በስህተት በጽሁፌ ላይ ስህተት የታያችሁ ሁሉ በአደባባይ ላይ ከመውቀስ አትቆጠቡ ምክንያቱም ከወቀሳው የምማረው አለና ነው::

ነጻነት ለአገራችንና ለህዝባችን <tamirat.yegezu@gmail.com>